የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

# ስትራቴጂክ ዕቅድ

## 2014 - 2018

## ማውጫ


መግቢያ ......2

መነሻ ......2

የኮሚሽኑ ተግባራት፣ ሥልጣን እና ኃላፊነቶች ......2

እሴቶችና መርሆዎች ......2

የሁኔታዎች ትንተና ......2

አዲስ መወቅር እና አዲስ አቅጣጫ ......6

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ተቋማዊ መዋቅር ......6

የወደፊት አቅጣጫ፦ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ......7

የባለድርሻ  አካላት ትንተና ......8

የጠንካራ ጎኖች፣ ድክመቶች፣ መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች ትንተና ......9

ስትራቴጂካዊ ትኩረት ......10

ራዕይ ......10

ተልዕኮ ......10

ተቋማዊ እሴቶች ......10

ቁልፍ የውጤት መስኮች ......10

የፕሮግራም መስኮች ......11

የፕሮግራም መስክ 1: የሰብአዊ መብቶች አስተምህሮት ......12

የፕሮግራም መስክ 2፡- የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ ......13

የፕሮግራም መስክ 3፡ የሴቶችና ሕጻናት መብቶች ......14

ፕሮግራም መስክ 4፡ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች ......15

የፕሮግራም መስክ 5፡- የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞችና ፍልሰተኞች መብቶች ......16

የፕሮግራም መስክ 6፡- የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ......18

የፕሮግራም መስክ 7፡- የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ መብቶች ......19

የፕሮግራም መስክ 8፡- ውጤታማ ኮሙኒኬሽን እና አጋርነት ......20

የፕሮግራም መስክ 9፡- የተቋማዊ ሪፎርም፣ አቅም ግንባታና ዘላቂነት/ቀጣይነት ......21

# መግቢያ

## መነሻ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌደራል ሕገ መንግስቱ መሰረት ነጻ ፌደራላዊ መንግስት አካል ሆኖ የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበርና እና ጥበቃ የሚሰራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። (የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55/14 እና አዋጅ ቁጥር 210/1992 በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው።)

## የኮሚሽኑ ተግባራት፣ ሥልጣን እና ኃላፊነቶች

በማቋቋምያ አዋጅ ቁጥር 210/1992 እና በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1224/2012 መሰረት ኮሚሽኑ ሕዝብ ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖረው ማስተማር፤ ሰብአዊ መብቶች መከበራቸውን እና መጠበቃቸውን የማረጋገጥ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ዋና ዋና ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፦

ሀ) ሕዝቡ ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖረው ማስተማር፣
ለ) ሰብአዊ መብቶች እንዳይጣሱ መጠበቅ፣ እና ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
ሐ) ሰብአዊ መብቶቹ ተጥሰው ሲገኙ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣

## እሴቶችና መርሆዎች

ኮሚሽኑ የተቋቋመለትን ተልዕኮ ለማሳካት የሚከተሉትን እሴቶች እና መርሆዎች ይከተላል፦

- ለእኩልነት፣ ለሰው ልጅ ክብር እና ፍትሕ ያለውን ቁርጠኝነት መሰረት በማድረግ የኮሚሽኑ አንኳር እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፦ ነፃነት/ገለልተኛነት፣ አካታችነት፣ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች እና ተጋላጭ የሕብረተሰቡ ክፍል ጋር አጋርነት፣ እውነተኝነትና እና ሥነ ምግባር የተላበሰ፤
- በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት እና ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ሰብአዊ መብቶች ሰነዶች እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና ሰብአዊነት ሕግጋት መመራት፤
- ACHPR/Res.370(LX)2017 ለብሔራዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና በአፍሪካ ውስጥ በተለይ በሰብአዊ መብቶች ላይ ለሚሰሩ ተቋማት የአጋር ተቋም ደረጃን ለመስጠት በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የወጣ የአቋም መግለጫ፣ እንዲሁም
- ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማትን በሚመለከት የወጡ መርሆዎች (የፓሪስ መርሆዎች) ማዕቀፎች ውስጥ መንቀሳቀስ፣

# የሁኔታዎች ትንተና

## ካለፈው ሂደታችን መማር

ኮሚሽኑ ከሃያ ዓመታት በፊት የተቋቋመ ይሁን እንጂ በወቅቱ በነበረው ፖለቲካዊ አስተዳደር እና ከባቢ ሁኔታ ምክንያት ተግባራቱን በሙሉ ነፃነት እና ውጤታማነት ማከናወን አልቻለም። ዓለም አቀፍ የብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ሕብረት አካል የሆነው የእውቅና ንዑስ ኮሚቴ እ.ኤ.አ በ2013 ኮሚሽኑ ስራውን በነፃነት የመስራትና ያለመስራት ብቃት ላይ ምርመራ/ምዘና አድርጎ ነበር። በዚህም መሰረት ኮሚሽኑ በነፃነቱ ረገድ ከነበሩት እና ትኩረት የሚሹ ነጥቦች የተነሳ የተሰጠው እውቅና ቢ (B)[1] ብቻ ነበር። እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ እ.ኤ.አ. ሜይ 14 2019 በተከናወነው በሦስተኛው "የዩንቨርሳል ፔሪዮዲክ ሪቪው" ወቅት ለኢትዮጵያ መንግስት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል ከተሰጡት 326 ምክረ

---

[1] [illegible]

ሃሳቦች መካከል 22ቱ የኮሚሽኑን ማቋቋምያ አዋጅ ማሻሻልን እና የኮሚሽኑን ሰብአዊ መብቶች ለማስፋፋት እና ለማስጠበቅ የሚያስችለውን ነፃነት እና ብቃት ማጎልበትን የሚመለከቱ ነበሩ፡፡

## እስከ 2011 ዓ.ም. የነበሩ ቁልፍ ተግዳሮቶች

በ2011 የተጀመረውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ አዲስ ዋና ኮሚሽነር እ.ኤ.አ በ2019 የተሾመ ሲሆን የተቋሙ ኮሚሽነሩም ተቋሙ እ.ኤ.አ 2020-2021 ሊከተለዉ የሚገባዉን አዲስ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

**የማቋቋሚያ አዋጅ፡-** ምንም እንኳን አዋጁ የሰብአዊ መብት ጥሰት ያደረሱ ባለግዴታዎች ላይ ጫና ለማሳደር የማጋለጥ እና የማሳጣትን ዘዴ የሚፈቅድ ቢሆንም ኮሚሽኑ የሚሰጣቸው ምክረ ሃሣቦች አተገባበርን በተመለከተ በርካታ ክፍተቶች ነበሩ፡፡

**አመራር እና ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ፡-** እስከ 2012 ዓ.ም. የነበረው የኮሚሺነሮች ሹመት የኮሚሽኑን ነፃነት እና ስራ አፈጻጸም በሚያውክ መልኩ በፖለቲካ ወገንተኝነት ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ የቀድሞ የኮሚሽኑ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ሁሉን አሳታፊ አልነበረም፡፡ የቀድሞ አመራርም የኮሚሽኑን ስልጣን ለመተርጎምም ሆነ በነፃነት ለመተግበር ብቃቱም ሆነ ቁርጠኝነቱ አልነበረውም፡፡

**የገንዘብ እጥረት፡-** ለኮሚሽኑ በፓርላማ የሚመደበው በጀት በፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተይዞ በየወሩ የሚለቀቅ ነበር፡፡ በመሆኑም ኮሚሽኑ የበጀት ማነስ እና የፋይናንስ ነፃነት ችግርም ነበረበት፡፡

**ተቋማዊ መዋቅር፡-** የኮሚሽኑ ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅም ተመሳሳይ ባህሪያት ካላቸዉ አቻ ተቋማት ጋር እንኳን ሲነጻጸር ብቁ እና ተፈላጊውን መመዘኛ የሚያሟሉ ባለሞያዎችን ለመሳብም ሆነ ለማቆየት በሚያስችል መጠን ተወዳዳሪ አልነበረም፡፡ የአካል ጉዳተኛ እንዲሁም የሴት ባለሞያዎች ቁጥርም በእጅጉ ያነሰ ነበር፡፡

**የጎንዮሽ እና ከታች ወደላይ ትብብር፡-** በዋናው እና በቅርንጫፍ ቢሮዎች መካከል የነበረው ቅንጅት ደካማ ነበር፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያት እቅድን፣ ትግበራን እና ክትትልን በተሳካ ሁኔታ ማከናወን የሚያስችል ግልጽ የአስተዳደር መዋቅር ወይም የአሰራር መንገድ አለመኖሩ ነው፡፡

**አካላዊ ተደራሽነት፡-** አብዛኞቹ የኮሚሽኑ ቢሮዎች ለሕዝብ በተለይ ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች እና ለአረጋውያን ተደራሽ አይደሉም፡፡ ከአገሪቱ የሕዝብ ብዛት መጠን፣ የቆዳ ስፋት እና ከሚከሰቱት የሰብአዊ መብት ጉዳዮች ስፋት አንጻር በዋና ዋና ከተማዎች ብቻ ተወስነው የሚገኙ ቢሮዎች ለብዙሃኑ ህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡

**አስቸኳይ ለሆኑ የሰብአዊ መብት ጉዳዮች ምላሽ ሰጪነት፡-** ኮሚሽኑ ለከባድ እና አስቸኳይ ለሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አቅም አልገነባም፡፡ በሌላ መልኩ የውስጣዊ ሂሳብ አሰራሮች/ሥርዓቶች ኮሚሽኑ ለአስቸኳይ የሰብአዊ መብት ሁኔታዎች አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ አይደሉም፡፡

**ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለ ትስስር/ግንኙነት፡-** በርካታ ገደብ ይጥል በነበረው የሲቪል ማህበረሰብ ሕግ ምክንያት ኮሚሽኑ ከሲቪል ማህበረሰቡ ጋር የነበረው ትብብር ውስን ነበር፡፡ እንዲሁም ከዓለም አቀፋዊ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ጋር የነበረው ግንኙነት ውስን ነበር፡፡

**የሰራተኞች ብቃት እና ክህሎት፡-** የብቃትና አቅም ማነስ በኮሚሽኑ የተለያዩ ክፍሎች እና ተግባራት ዘንድ ዘወትር የሚነሳ ጉዳይ ነው፡፡ በተለያዩ የሰብአዊ መብት ጭብጦች፣ ፕሮጀክት ቀረጻ፣ ትግበራ እና ክትትል፣ ውጤቶችን ማሰባሰብ፣ ስርዓተ ጾታ ማስረጽ እና አካታችነትን በተመለከተ የእውቀት እና ክህሎት ውስንነት ነበረ፡፡

**ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና ተሽከርካሪዎች፡-** ኮሚሽኑ ለተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለመድረስ እንዲሁም ክንውኖችን በብቃት ለመፈጸም በቂ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና

የሎጂስቲክስ ብቃት የለውም። የዕለት ተዕለት ተግባራት ለመከወን እንቅፋት ናቸው ተብለው ከተለዩ ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ የተሽከርካሪ እጥረት ነው። ኮሚሽኑ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ነፃ የስልክ አገልግሎት የለውም፣ ድረ ገፁም በሚገባ ተግባራዊ አልነበረም፣ የማይቆራረጥና ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት አገልግሎት አልነበረውም። ኮሚሽኑ በተለይ ምስጢራዊ የሆኑ ሰነዶች እና መረጃዎች በአግባቡ ለማስቀመጥ የሚያስችሉ ደህንነቱ የተጠበቀ እና የመረጃ ማቋቻ ስርዓት አልነበሩትም።

**ምርመራ እና አቤቱታ ማስተናገጃ ዳይሬክቶሬት፡-** ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምላሽ ለመስጠት የተሰጡ ምክረ ሃሣቦችን ትግበራ በተመለከተ የሚከናወነው ቀጣይ ክትትል እና ውትወታ እጅግ አነስተኛ ነበር።ኮሚሽኑ ለፓርላማ የሚያቀርበውን ዓመታዊ ዘገባውን ምክረ ሀሳቦቹን ለመተግበር ዳተኛ በሆኑ ባለግዴታዎች ላይ ጫና ለማሳደር አይጠቀምበትም ነበር። በዚህም ምክንያት የተለያዩ አካላት በተለይ መንግስታዊ አካላት የኮሚሽኑን ምክረ ሃሳብ ከቁብ አይቆጥሩትም ነበር።በፆታ የተከፋፈለ የአቤቱታ አቅራቢዎች መረጃ እንደሚያሳየው ከሆነ የሴት አቤቱታ አቅራቢዎች ቁጥር ከወንዶች እንደሚያንስ፣ የአካል ጉዳተኛ አቤቱታዎች አቅራቢዎች ከዛም በጣም እንደሚያንስ እንዲሁም በሕፃናት ምንም አይነት አቤቱታ እንደማይቀርብ ያሳያል። ማዕከላዊ የሆነ የመረጃ ቋት፣ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር (case management) ስርዓት የለም። በመሆኑም መረጃ ማሰባሰብ፣ ምዝገባ እና ትንተና የመሳሰሉ ተግባራት በእጅ የሚተገበሩ ብሎም ከፍ ያለ የሰው ሃይል የሚጠይቁ ተግባራት ናቸው። የኮሚሽኑ ነፃ የስልክ አገልግሎት በተለያዩ ጊዜያት ኢትዮ ቴሌኮም አገልግሎቱን በማቋረጡ፣ የቀጥታ መስመር /ሆት ላይን/ አማካሪዎች ስራ በመልቀቃቸው እና ከኔትዎርክ ጋር በተያያዘ ምክንያት አገልግሎቱ መቆራረጥ ደርሶበታል።

**የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ እና ክትትል ዳይሬክቶሬት፡-** የክትትል ሥራ የትኩረት አቅጣጫን፣ የውትወታን ሥራ፣ አጋርነትን እና ትብብርን በተመለከተ ግልጽ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫ አልነበረም። የክትትል ዘገባዎች ተጠናቀው ለሕዝብ ይፋ የሚደረጉበት አጋጣሚ አነስተኛ ነበር። የስነዳ ተግባራት ደካማ ናቸው። ይህም በመሆኑ ያለፉ የክትትል መረጃዎችን እና ምክረሃሳቦችን ለማውጣት አስቸጋሪ ነው። ሌሎች ማለትም ሕፃናት ማሳደጊያዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማት፣ የአረጋውያን እንክብካቤ ማዕከላት፣ ከመኖርያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ማዕከላት እና በመሳሰሉ ቦታዎች የነበረው ክትትል እጅግ በጣም ውስን ነበር።

ኮሚሽኑ ነባር ሕግጋት እንዲሻሻሉ እንዲሁም አዳዲስ ሕግጋት እንዲወጡ በማድረግ ረገድ የነበረው ተሳትፎም በጣም የተወሰነ ነበር። በአገሪቱ ውስጥ ስላለው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በመደበኛ ሁኔታ ክትትል በማድረግ ለሕግ አውጪው መረጃ የሰጠበት አጋጣሚም እጅግ በጣም አናሳ ነው። ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መብቶችን በተመለከተ በኮሚሽኑ እስከአሁን ድረስ የተሰራው ስራም እጅግ በጣም ውስን ነው። የተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት የክትትል አካላት የሰጧቸውን የመደምደምያ ሃሣቦች ትግበራ ለመከታተል የተከናወኑ ተግባራት ሲበዛ ውስን ናቸው። የክትትል ሥራውን በሰብአዊ መብቶች ላይ ከፍተኛ ተፅዕና ከሚያሳድሩ ዘላቂ የልማት ሂደቶች ጋር ለማገናኘት የሚደረጉ ጥረቶች አልነበሩም። ኮሚሽኑ ከዓለም አቀፍ እና ከአጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስርዓቶች ጋር ያለው ግንኙነት በጣም ውስን ነው።

**ሴቶች፣ ሕፃናት እና ሌሎች ለመብት ጥሰት የተጋለጡ ሕብረተሰብ ክፍሎች ዳይሬክቶሬት፡-** ይህ ዳይሬክቶሬት እንደ ሌሎቹ የስራ ክፍሎች ሁሉ ብቃት ያላቸው ባለሞያዎች፣ ግብዓቶች፣ መመርያዎች፣ ፖሊሲዎች፣ ስርዓቶች እና መሳርያዎች እጥረት አለበት። ዳይሬክቶሬቱ ዘላቂ የልማት ግቦች ከፆታ እኩልነት አኳያ ምን ያህል ስኬታማ መሆናቸውን የሚከታተልበት ስርዓት የለውም። ዳይሬክቶሬቱ ስርዓተ ፆታ በሁሉም የኮሚሽኑ ዋና ተግባራት ውስጥ ማስረጽን፣ ለሕፃናት ምቹ እንዲሁም አካል ጉዳተኝነትን አካታች እንዲሆን እንዲሁም በኮሚሽኑ ሰራተኞች በተለይም በባለሞያ እና ከፍተኛ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመጣጣኝ የፆታ ውክልና እንዲኖር


አልሰራም። ምንም እንኳን የስራ ክፍሉ የሌሎችን ተጋላጭ ወገኖች ማለትም አካል ጉዳተኞችን፣ አዛውንቶችን፣ ተፈናቃዮችን ወዘተ ማራመድ እና መብቶችን ማስጠበቅ ቢጠበቅበትም በዚህ ረገድ የተሰራው ሥራ ውስን ነው።

**የሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እና አስተምህሮት ዳይሬክቶሬት፡-** ኮሚሽኑ ውጤታማ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል ማዕቀፍ እና አቅጣጫ የሚያስቀምጥ የአተገባበር መለኪያ ደረጃ አልነበረውም። መመርያዎቹ ጽንሰሃሳባዊ እና ተጨባጭ/እውነተኛ/ነባራዊ ሁኔታዎችን የማያንጸባርቁ፤ አብዛኞቹ መመርያዎች የአሳታፊ ትምህርት ዘዴ የማይከተሉና ለአጠቃቀምም ምቹ ያልነበሩ ናቸው። ኮሚሽኑ የሰብአዊ መብቶች ስልጠናውን የመጨረሻ ውጤት አይለካም ነበር።

# አዲስ መወቅር እና አዲስ አቅጣጫ

## የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ተቋማዊ መዋቅር

ኮሚሽኑ በ2012 ከጀመረው የማሻሻያ ተግባራት ውስጥ አንዱ የተቋም አደረጃጀት፣ የስራ ምዘና እና የደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ስርዓቱ ላይ ምርመራ/ግምገማ ማድረግ ሲሆን የምርመራው ጠቅላላ ዓላማ የኮሚሽኑን አጠቃላይ ተልዕኮ፣ ሚና እና ኃላፊነት የሚያንጸባርቅ ውጤታማ የተቋም አደረጃጀት ለመቅረጽ እና ለማቋቋም ነው፡፡ የአዲሱ አደረጃጀት ጠቅላላ ገጽታ እንደሚከተለው ነው፡-



## የወደፊት አቅጣጫ፡ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ

### የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ፣ አካባቢያዊና ሕጋዊ ሁኔታዎች ትንተና

| ሁኔታዎች | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|
| ፖለቲካዊ | • ኮሚሽኑን ለመለወጥ ግልጽ የፖለቲካ ቁርጠኝነት እና በኮሚሽኑ የሚሰጡ ምክረሃሣቦችን ለመተግበር በመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት የኢፌዲሪ ፕሬዝደንቷን፣ ጠቅላይ ሚንስትሩን፣ የክልል መንግስታትን ጨምሮ ሌሎች የመንግስት ኃላፊዎች እና የማህበረሰብ መሪዎች ያሳዩት ተነሳሽነት<br>• ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር ግልጽ የመንግስት ቁርጠኝነት<br>• ለሴቶች እና ለሕፃናት የተሰጠ ከፍ ያለ ትኩረት<br>• የሰፋ የፖለቲካ ምህዳር እና የሲቪክ ማህበራት ተሳትፎ | • የጸጥታ እና የደህንነት ስጋት እንዲፈጠር ምክንያት የሆኑ የፖለቲካ ጽንፈኝነቶች<br>• ብሔርን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ አስተሳሰብ እና በሰብአዊ መብቶች መካከል ያለ ተቃርኖ<br>• በአንዳንድ ክልሎች የሚስተዋል መድሎአዊ አሰራር<br>• በአንዳንድ ክልሎች እየታየ ያለ ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር ያለ ተነሳሽነት መቀነስ<br>• የዘላቂ ልማት ሂደቶችን የሚያካትት ሰብአዊ መብቶችን መሠረት ያደረገ ክትትል ማድረግ ላይ የግንዛቤ ማነስ |
| ኢኮኖሚያዊ | • አገር በቀል የሆነ ምርታማነትን በማጎልበትና ሰፊ የዕድገት መሰረት ላይ የሚያተኩር የኢኮኖሚ ፖሊሲ<br>• በግል ዘርፍ ላይ ትኩረት የሚሰጥ ነጻ ኢኮኖሚ ለማራመድ ያለ ፍላጎት<br>• ድሆችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ<br>• ወጣት እና ምርታማ የሆነ ማህበረሰብ<br>• ኮሚሽኑ የአዲሱን የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ የክትትል ማዕቀፍ ከሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ከዘላቂ ልማት ግቦች አመላካች ማዕቀፍ ጋር እንዲጣጣም ተጽዕኖ ለማሳደር ያለው እድል | • የልማት ዕቅድ እና ትግበራ ሰብአዊ መብቶች ተኮር አለመሆን<br>• ከፍተኛ ስራ አጥነት<br>• የኑሮ ውድነት እና ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት<br>• የውጭ አገር ውዝፍ ዕዳ<br>• የአገር የምንዛሪ ተመን ማሽቆልቆል<br>• ከልማትና ግጭት ጋር የተያያዙ መፈናቀሎች<br>• ከፍተኛ የሆነ ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት/ዝውውር<br>• ድህነት<br>• የኢኮኖሚ ዕድገት መቀነስ<br>• መደበኛ ያልሆነ ሰፈራ እና የግዳጅ መፈናቀል |
| ማህበራዊ | • የተሻሻለ የትምህርት እና የጤና ተደራሽነት<br>• በአደጋ ጊዜ የሰዎች የመደጋገፍ ባህል<br>• ማህበረሰቡ ለተፈናቃይ ሰዎች የሚያደርገው በጎ አስተዋጽዖ<br>• ለመገናኛ ብዙኃን እና ለሲቪክ ማህበራት የተሰጠ ነፃነት<br>• በሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ላይ ያለ የተሻሻለ ግንዛቤ<br>• የማህበረሰብ ተደጋጋፊነት | • ከፍተኛ የአለመማር ምጣኔ<br>• ሰፊ የሆነ ሙስና እና ብልሹ አሰራር<br>• ደረጃቸውን ያልጠበቁ የትምህርት እና የጤና አገልግሎቶች<br>• ፈጣን የሕዝብ ብዛት ዕድገት<br>• የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተጽዕኖ<br>• በድርቅ ምክንያት የሚከሰት ረሃብ<br>• ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት/ዝውውር<br>• ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና ሕገወጥ የድንበር መሻገር<br>• በሴቶች እና ሕፃናት ላይ የሚፈጸም ጥቃት<br>• የስርዓተ ጾታ እኩልነት አለመስፈን<br>• የማህበራዊ ዋስትና ደካማነት<br>• በአረጋውያን እና በአካል ጉዳተኝነት ላይ ያለ የተዛባ አመለካከት እና ማግለል<br>• የዘላቂ ልማት ግቦችን ያማከለ የክትትል |

| ሁኔታዎች | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
|---|---|---|
| | | ስርዓት አለመኖሩ |
| ቴክኖሎጂያዊ | • የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መስፋፋት<br>• የመረጃ ተደራሽነት መሻሻል<br>• የሰብአዊ መብቶች ባህልን ማጎለበት የሚያስችሉ መረጃ መለዋወጫ የበየነ መረብ መድረኮች እና ማህበራዊ ሚዲያ መስፋፋት<br>• የመንግስት አገልግሎቶች በድረገጾች አማካኝነት ተደራሽ መሆን<br>• ዲጂታል የስራ ዕድል ከመብት አንጻር<br>• የዲጂታል ኢኮኖሚ በአስር አመቱ የልማት ዕቅድ የተሰጠው ትኩረት<br>• የኢንተርኔት ንግድ በምስራቅ አፍሪካ መስፋፋት | • የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መስፋፋት በግለሰቦች የግል ሚስጥር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ<br>• በማህበራዊ ሚዲያ ምክንያት የሚመጣ የጥላቻ ንግግር እና ጽንፈኝነት መስፋፋት<br>• የማህበራዊ ሚዲያ ጽንፈኝነትን/አክራሪነትን የማስፋፋት ዝንባሌ<br>• የዳታ ጥበቃ አለመኖር<br>• በድረገጽ የሚፈጸም ጥቃት |
| ህጋዊ | • ሰብአዊ መብቶች በሕገ መንግስቱ ጥበቃ የተሰጣቸው መሆኑ<br>• የተለያዩ ዓለም አቀም የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች መጽደቃቸው<br>• የኮሚሽኑ የማቋቋሚያ አዋጅ እንዲሻሻል መደረጉ<br>• ለሰብአዊ መብቶች አዎንታዊ አስተዋጽዖ ያላቸው ሰፊ የሕግ ማሻሻል ስራዎች | • አንዳንድ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ኢትዮጵያ አለማፅደቋ<br>• አንዳንድ የአገር ውስጥ ሕጎች ከዓለም አቀፍ እና ሀጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር አለመጣጣም<br>• በአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዙሪያ የሕግ ማዕቀፍ አለመኖሩ<br>• የፍትሕ አገልግሎት ተደራሽ አለመሆን<br>• ለመብት ጥሰቶች በቂ የሆነ ካሳ አለመሰጠት<br>• በዓለም አቀፍ እና በሀጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎች የሚሰጡ ምክረ ሃሣቦች በአግባቡ አለመተግበር |
| አካባቢያዊ | • ሰፊ የችግኝ ተከላ እና የአካባቢያዊ ማሻሻል ስራዎች<br>• የአረንጓዴ አሻራ እንቅስቃሴ<br>• ለአካባቢ ጥበቃ እና ለአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ የጨመረ የዓለም አቀፍ እና ሀጉራዊ ትኩረት | • አካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ስራዎች የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አለመጠናት<br>• ፋብሪካዎች እና የኢንዱስትሪ ፓርኮች አስተዳደርን የሚመለከት ጥብቅ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ አለመኖር<br>• የካርቦን ልቀት ላይ በአግባቡ ቁጥጥር አለመደረጉ<br>• የአገር ውስጥ የአደጋ ዝግጁነት እና የቅድመ መከላከል ስራ ደካማ መሆን |

## የባለድርሻ አካላት ትንተና

እንደ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ኮሚሽኑ በዓለም አቀፍ እና በአገር ውስጥ ባሉ ሁኔታዎች ላይ፣ በመንግስት ተቋማት መካከል እንዲሁም በመንግስት እና በሲቪክ ተቋማት ብሎም በመብቶች መካከል ልዩ የሆነ የመገናኛ ድልድይ የመፍጠር ሚና አለው፡፡ ኢሰመኮ ከሰብአዊ መብቶች ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በውሳኔዎች ላይ ምክረሃሳብ በመስጠት እና የውሳኔ ሂደቶች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ቁልፍ ሚና ለመጫወት ይሰራል፡፡ ኢሰመኮ በሰብአዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት፣ የንግድ ተቋማት እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት ጋር በመተባበር የሰብአዊ መብቶች ዋና እና ገለልተኛ አገር አቀፍ ማዕከል ለመሆን ይሰራል፡፡

ከዚህም አንጻር የባለድርሻ አካላት ትንተና የተሰራ ሲሆን በዚህም ስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ሲሰራ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት እና ከኮሚሽኑ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመተንተን የሚያስችሉ

መረጃዎች ተሰብስበው ውይይት ተካሂዶባቸው ከኮሚሽኑ ስራ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ተለይቷል፡፡ ኢሰመኮ ይህን መረጃ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመቃኘት እና ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትብብር ለማጎልበት ይጠቀምበታል፡፡

### የጠንካራ ጎኖች፣ ድክመቶች፣ መልካም አጋጣሚዎች እና ስጋቶች ትንተና

የኮሚሽኑን ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች ለመተንተን የጥንካሬ፣ የድክመት፣ የመልካም አጋጣሚዎች እና የስጋት ትንተና በኮሚሽኑ ሰራተኞች እና ከኮሚሽኑ ውጪ ባሉ አካላት ተሰርቷል፡፡ ኢሰመኮ ጥንካሬዎቹን በመመርኮዝ፣ መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም እንዲሁም ስጋቶችን በመቀነስ እና ድክመቶችን እንዲሻሻሉ በማድረግ የተሻለ ተቋም እንዲሆን ይሰራል፡፡ ከዚህ የሚከተሉት የኮሚሽኑን የጠድመስ ትንተና ያሳያሉ፡፡

| ጠንካራ ጎኖች | ድክመቶች |
|---|---|
| • ለኢሰመኮ በሕገመንግስቱ የተሰጠ ስልጣን<br>• በተሻሻለው አዋጅ የተሰጠ የሰፋ ስልጣን<br>• በስትራቴጂካዊ ዕቅድ ዝግጅት እና ትግበራ ላይ ያለ ልምድ<br>• የተወሰነ ማንዋል፣ ቼክሊስት እና መመሪያዎች መኖር<br>• በአገር አቀፍ እና በክልሎች ደረጃ የተዋቀረ መሆን<br>• በመጎለበት ላይ ያለ ተቋማዊ ነፃነት<br>• ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ውጤት እያሳዩ እንዲሁም ለሕዝብ ታዋቂ እየሆኑ የመጡ የኮሚሽኑ ስራዎች<br>• ትጉህ ሰራተኞች መኖራቸው | • በዋናው እና በክልል ጽ/ቤቶች ያለ የትብብር እና የቅንጅት መላላት<br>• ያለፈው ዕቅድ አሳታፊ አለመሆን እና ደካማ ትግበራ<br>• ውጤታማ ያልሆነ የክትትል እና የግምገማ ማእቀፍ<br>• ምቹ ያልሆነ የስራ ሁኔታ እና ለሰራተኞች ያለ አነስተኛ ማነቃቂያ ማዕቀፍ (በክፍያ፣ በጥቅማ ጥቅም፣ በስልጠና ወዘተ…)<br>• በቀደመው የፖለቲካ አስተዳደር የነበረ ጣልቃ ገብነት<br>• ግልጽ ያልሆነ የሰራተኞች የስራ ድርሻ እና ተመሳሳይነት ያላቸው የስራ ክፍፍሎች<br>• የሰራተኞች አመዳደብ ብዝኃነትን ያገናዘበ አለመሆን (ለምሳሌ ከጾታ፣ ከብሔር ተዋጽዖ እና አካል ጉዳተኞችን ከማካተት አንጻር)<br>• ውስን ተደራሽነት፣ የኪራይ ቤት መጠቀም፣ ለተገልጋዮች በተለይ ለአካል ጉዳተኞች እና ለአረጋውያን ተደራሽ አለመሆን<br>• ውስን/በቂ ያልሆኑ ሀብቶች እና ሎጅስቲክስ<br>• ስለ ተልዕኮው የግንዛቤ እጥረት፣ የኮሚሽኑ ስራ ብዙም የሚታወቅ የሚታይ ያለመሆኑ ሁኔታ<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለ ውስን የሆነ የትብብር ሁኔታ<br>• ለአገር አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ተቋማት ደረጃ በሚሰጠው አካል (Sub-Committee on Accreditation of GANHRI) የ ቢ ደረጃ ላይ መሆን |
| **መልካም አጋጣሚዎች** | **ስጋቶች** |
| • ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር ግልፅ የፖለቲካ ቁርጠኝነት<br>• ኮሚሽኑን ለመለወጥ እና ለማጠናከር በመንግስት በኩል የታየ ቁርጠኝነት<br>• በሲቪል እና በፖለቲካ መብቶች ዙሪያ ያለ ግንዛቤ ማደግ<br>• ለሰብአዊ መብቶች አከባበር በጎ አስተዋጽዖ ያላቸው ሰፊ የሕግ ማሻሻል ስራዎች<br>• የልማት አጋሮች ለሰብአዊ መብቶች አከባበር መሻሻል እና ለኮሚሽኑ ስራዎች የሚያሳዩት ሰፊ ድጋፍ<br>• በአህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የሰብአዊ | • በፖለቲካ ጽንፈኝነት ምክንያት የሚከሰት የሰላም እና ጸጥታ መደፍረስ<br>• ጽንፈኝነትን የሚያባብሱ የማህበራዊ ሚዲያዎች መስፋፋት<br>• ለሰብአዊ መብቶች መከበር በአንዳንድ ክልሎች የሚታይ ዝቅተኛ የፖለቲካ ፍላጎት<br>• የዋጋ ንረት እና የኢኮኖሚ ዕድገት ማነስ<br>• ከፍተኛ ስራ አጥነት<br>• ሙስና<br>• የኢሰመኮ ምክረ ሃሣቦች ሙሉ በሙሉ አለመተግበር<br>• አናሳ የፍትሕ ተደራሽነት<br>• የተጠያቂነት አለመኖር እና ኃላፊነት የመውሰድ አናሳነት |

| | |
|---|---|
| መብቶች ማስፈጸሚያ ማዕቀፎች<br>• የሲቪክ ተቋማት ተሳትፎ እና የፖለቲካ ምህዳር መስፋት<br>• በድረገጽ የሚሰጡ አገልግሎቶች መስፋፋት<br>• የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመር | • ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በቂ የሆነ መፍትሄ አለማግኘት<br>• የፍርድ ቤት ትዕዛዞች በአስፈጻሚው አካል በአግባቡ አለመተግበር<br>• ማህበረሰቡ በፍትሕ ስርዐቱ ላይ አመኔታ ማጣት |

## ስትራቴጂካዊ ትኩረት

ይህ ክፍል የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ስትራቴጂካዊ ትኩረቶችና የተቋማዊ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ (የለውጥ ንድፈሃሳብ) ይገልጻል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኮሚሽኑን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ ስትራቴጂካዊ ግቦች እና ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ ዋና ዋና ፕሮግራሞችን (መርሃ ግብሮች) ይገልጻል፡፡

### ራዕይ

**የሰብአዊ መብቶች ባህል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት**

### ተልዕኮ

**የሰብአዊ መብቶች ጥበቃን ለሁሉም ማረጋገጥ እና ማራመድ (ማስፋፋት)**

### ተቋማዊ እሴቶች

**ለእኩልነት፤ ለሰብአዊ ክብር እና ለፍትሕ ያለንን ቁርጠኝነት መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፡-**

| | |
|---|---|
| **ተቋማዊ ነጻነት** | ኢሰመኮ የመንግስት ተቋም ቢሆንም በተቋማዊ ነጻነት መርህ የሚሠራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ነው፡፡ ነጻና ገለልተኛ አመራርን፤ ባለሙያ የሆኑ ሰራተኞችን እና የፋይናንስ አጠቃቀም ነጻነትን በመጠቀም ኮሚሽኑ ከመንግስት አስፈጻሚ አካላት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከሌሎች አካላት ያለውን ነጻነትን ያስጠብቃል፡፡ |
| **አካታች** | የአመራርና የሰራተኛ ጥንቅራችን ብዝሃነት ያለውና አካታች እንዲሆን እንጥራለን፡፡ እንዲሁም በተልዕኳችንና በተግባር ኃላፊነታችን አድሎንና መገለልን ለማስወገድ እንሰራለን በዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዝሃነት እናንጸባርቃለን፡፡ |
| **አጋርነት - ከተጎጂዎች / ለጉዳት ተጋላጭ ከሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር** | የሰብአዊ መብት ጥሰት ከደረሰባቸውና ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ ከሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ጎን በመቆም መብታቸውን እንዲጠይቁ እና እንዲጠቀሙ እናበቃለን፡፡ ድጋፍ እናደርጋለን፡፡ |
| **በእውነተኛነት እና በሥነ ምግባር የታነጸ** | ሥራዎቻችንን እና የምናቀርባቸውን የመፍትሄ ሃሣቦች (ምክረ ሃሣቦቻችን) በእውነታ እና ማስረጃ ላይ እንዲመሠረቱ አስፈላጊውን ጥረት እናደርጋለን፡፡ የሙያ ሥነ ምግባሮችን፤ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በከፍተኛ ደረጃ እንጠብቃለን፡፡ |

## ቁልፍ የውጤት መስኮች

በዚህ የስትራቴጂክ ዕቅድ ትግበራ ዘመን ኮሚሽኑ በሕግ የተሰጠውን ተግባር፤ ኃላፊነትና ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችሉና ተቋማዊ ብቃቱን የሚያጎለብቱ አምስት ቁልፍ የውጤት መስኮች/ስትራቴጂክ ግቦች ላይ አትኩሮ ይሰራል፡፡

<table>
<tr>
<td rowspan="5">ቁልፍ የውጤት መስኮች</td>
<td>ቁልፍ የውጤት መስክ 1፡ ውጤታማ የሰብአዊ መብቶች አስተምህሮት<br>ባለመብቶች እና ባለግዴታዎች የሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ ያላቸውን ዕውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት በማሳደግ ሰብአዊ መብቶችን ባህል ማድረግ፤</td>
</tr>
<tr>
<td>ቁልፍ የውጤት መስክ 2፡ የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራን ማጎልበት<br>ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ደረጃዎች መከበራቸውን እና ጥሰቶችም በትክክል ምርመራ ተከናውኖባቸው ተገቢ የሆነ ማካካሻ/ማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን እና አጥፊዎችም ተጠያቂ መደረጋቸውን ማረጋገጥ፤</td>
</tr>
<tr>
<td>ቁልፍ የውጤት መስክ 3፡ ቁልፍ በሆኑና ቅድሚያ በሚሰጣቸው መስኮች የሰብአዊ መብቶችን ማጎልበት<ul><li>የሴቶችና ሕጻናት መብቶች</li><li>የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች</li><li>የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞች እና ፍልሰተኞች መብቶች</li><li>የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች</li><li>የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ መብቶች</li></ul>ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ በሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችና ቁልፍ በሆኑ የሲቪል ነጻነትና የኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶች ላይ በማተኮር የሰብአዊ መብቶችን ጥበቃ እና መስፋፋትን ማረጋገጥ፤</td>
</tr>
<tr>
<td>ቁልፍ የውጤት መስክ 4፡ ውጤታማ ኮሙኒኬሽን ኢኮቴና አጋርነት<br>እውቅናን እንዲሁም ከሕብረተሰብና ቁልፍ ከሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር መስተጋብርን/ትብብርን በማሳደግ ከፍ ያለ ውጤት የሚያመጣ የሰብአዊ መብቶች ተግባራትን ማከናወን፤</td>
</tr>
<tr>
<td>ቁልፍ የውጤት መስክ 5፡ ተቋማዊ ሪፎርምና በዘላቂነት ማጠናከር<br>የኮሚሽኑን ተልዕኮ፣ተግባርና ኃላፊነቱን የሚመጥን ነጻ፤ ውጤታማ እና ዘላቂነት ያለው ተቋም እንዲሆን ማስቻል፤</td>
</tr>
</table>

## የፕሮግራም መስኮች

ኮሚሽኑ አምስቱን ቁልፍ የውጤት መስኮች ዕውን ለማድረግ ሰፋፊ ሰብአዊ መብቶችን የማራመድና የማስጠበቅ ስራዎችን በዘጠኝ ፕሮግራሞች ስር በማደራጀት ይተገብራል፡፡ ዘጠኙ ፕሮግራሞች በየሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች አማካይነት እንዲሁም ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር በተቀናጀ መንገድ ብሎም ቁልፍ የውጤት መስኮችን ለማሳካት ከተለያዩ አገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከሌሎች አገራት ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ጋር አስፈላጊ ህብርና ቅንጅት በመፍጠር ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

**የፕሮግራም መስክ 1: የሰብአዊ መብቶች አስተምህሮት**

**የስትራቴጂው ዓላማ፡** ባለመብቶች እና ባለግዴታዎች ሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ ያለቸውን ዕውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት በማሳደግ ሰብአዊ መብቶችን ባህል ማድረግ

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (outcomes) | የአፈጻጸም አመላካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 1.1. **ሕብረተሰቡ ለጉዳት የተጋለጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን ጨምሮ ስለ ሰብአዊ መብቶች ያለውን ግንዛቤና ትምህርት /እውቀት/ ማሳደግ** | • በበየነ መረብ ትምህርት (online training)ን ጨምሮ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት መርሃግብሮችን ማዘጋጀትና መተግበር<br>• የምስለ ፍርድ ቤት ውድድር ማዘጋጀት<br>• በሰብአዊ መብቶች አስተምህሮት እንዲሳተፉ ሲቪል ማህበራትን ማብቃት | ሕብረተሰቡ ስለ ሰብአዊ መብት ያለዉ ግንዛቤ ጎልብቷል፤ ባለመብቶች እና ሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ሰብአዊ መብቶችን ለመጠየቅ የበቁ ይሆናሉ፡፡ | • ባለመብቶችን በተመለከተ የተዘጋጁ ተዛማጅ፣ ውጤታማና ጠቃሚ እንዲሁም ዘላቂ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት መርሃግብሮች (በበየነ መረብ ትምህርትን ጨምሮ) ብዛት በቁጥር<br>• ባለመብቶች የሰብአዊ መብት ጥሰት በሚያጋጥሟቸው ጊዜ ያደረጓቸው ሪፖርቶች ብዛት በመቶኛ<br>• ሰብአዊ መብትን ለማስከበር የተጠናከሩ የሲቢል ማህበረሰብ ተቋማት ብዛት በመቶኛ |
| 1.2. **የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በተመለከተ የቁልፍ ባለድርሻ አካላትን አቅም እና ቁርጠኝነት መገንባት** | • የሕግ አውጪ አካላትን፣ የብሔራዊና ክልላዊ አስተዳዳሪዎችን ትኩረት ሊሰጣቸዉ የሚገቡ የዘርፍ ሰብአዊ መብቶች፣ ሰብአዊ መብት ተኮር አሰራር እንዲሁም በዘላቂ የልማት ግቦች ዙሪያ ማሰልጠን<br>• ለቁልፍ የመንግስት ሰራተኞች እና የግል ዘርፉን ጨምሮ ባለግዴታዎችን ማሰልጠን<br>• ለባለግዴታዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና ማዘጋጀት (TOT) | ባለግዴታዎች ሰብአዊ መብቶችን ለማክበር፣ ለማስከበር እና ለማሟላት ያላቸው አቅምና ቁርጠኝነት ይጎለብታል | • ሰብአዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታ ያለባቸውን አካላት በተመለከተ ውጤታማና ጠቃሚ እንዲሁም ዘላቂ ትምህርታዊና ኢ-ትምህርታዊ የሆኑ የተዘጋጁ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት መርሃግብሮች ብዛት በቁጥር<br>• ባለግዴታዎች ሰብአዊ መብትን ለማክበር፣ ለመጠበቅና ለማስፋፋት የሚሆኑ ምላሽ ሰጪ እርምጃዎች ብዛት በቁጥር |
| 1.3. **የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት መርሃግብሮች ማካተት/ማስረጽ** | • የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በመጀመሪያ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በመምህራን እንዲሁም የተለያዩ የሙያ ስልጠና በሚሰጡ ተቋማት ውስጥ እንዲካተት መወትወትና ማስተባበር<br>• የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን የሚለመከተው የዘላቂ ልማት ግብ 4.7 አተገባበር ላይ ክትትል አድርጎ ዘገባ ማዘጋጀት<br>• ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት መርሃግብር እንዲኖር ውትወታ/ግፊት ማድረግ | የሰብአዊ መብቶች ትምህርት በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ ሥርዓተ ትምህርቶች እና የባለሞያዎች ስልጠና መመርያዎች ውስጥ በላቀ ሁኔታ/ደረጃ መካተት | የተካተቱ ተዛማጅ፣ ብቃት ያላቸው እና ዘላቂ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ትምህርት መርሃ ትምህርቶች ብዛት በቁጥር |
| 1.4. **በሰብአዊ መብቶች ትምህርት ረገድ መተባበርና መደጋገፍ** | • የሰብአዊ መብቶች ትምህርትን በተመለከተ አግባብነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መተባበር /በጋራ መስራት<br>• ከሌሎች የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና ጥምረቶች ጋር መስራት፣ በነዚሁ አካላት የተዘጋጁ መድረኮች ላይ መሳተፍ<br>• የልምድ ልውውጥ/ተሞክሮ ማጋራት ጉብኝቶች ላይ መሳተፍ እንዲሁም ማዘጋጀት | ኮሚሽኑ በሕግ አውጭው አካል፣ በትምህርት ባለስልጣናት በሲቪክ ማህበረሰብ እንዲሁም በዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ትምህርት ተቋማት እና መድረኮች መካከል ጠንካራ አገናኝ ድልድይ ነው፡፡ | ከኮሚሽኑ ጋር የሚሰሩ ተቋማትና ትስስሮችና ጥምረቶች ብዛት በቁጥር |
| 1.5. **የአመራርና ሠራተኞች** | • የሥልጠና ፍላጎት ጥናት ማድረግ | የሰብአዊ መብቶች ትምህርት | በየሥራ ክፍሉና በየጾታው የሰለጠኑና ብቁ አመራርና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አቅም ግንባታ | • የአመራርና ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• ሜንተሪንግ ኮቺንግና የሥራ ላይ ሥልጠናን ጨምሮ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን | መርሃግብሮችን ለመቅረጽ፣ ለመተግበር፣ ለመከታተል እና ለመገምገም የሚያስችል የጎለበተ አቅም ያለው አመራርና ሠራተኛ | ሠራተኛ ብዛት በቁጥር |

## የፕሮግራም መስክ 2፡- የሰብአዊ መብቶች ክትትልና ምርመራ

**የስትራቴጂው ዓላማ፡-** ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ደረጃዎች መከበራቸውን እና ጥሰቶችም በትክክል ምርመራ ተከናውኖባቸው ተገቢ የሆነ ማካካሻ/ማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን እና አጥፊዎችም ተጠያቂ መደረጋቸውን ማረጋገጥ

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (Outcomes) | የአፈጻጸም አመላካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 2.1.በጥበቃ ስር/እስር ላያ ያሉ ሰዎች አያያዝ የሚመለከቱ የሕግ ማዕቀፎች እንዲሻሻሉ ውትወታ/ግፊት ማድረግ | • በፌደራልና ክልል ደረጃ ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት በሕግጋት ላይ ምርመራ/ጥናት ማድረግ<br>• ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ምክረ ሃሳብ መስጠት እና ለተግባራዊነታቸዉ ውትወታ/ግፊት ማድረግ<br>• በሥራ ላይ ባሉ እንዲሁም በረቂቅ አዋጆችና ደንቦች ላይ አስተያየት ማቅረብ | በጥበቃ ስር/እስር ላይ ለሚገኙ ሰዎች የተሻለ የሰብአዊ መብት ጥበቃ የሚያደርጉ የሕግ ማዕቀፎች፤ | በጥበቃ ስር/በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎችን መብት ጥበቃ ለማሻሻል በተከለሱ ወይም በወጡ ሕጎች ውስጥ በኮሚሽኑ የተሰጡና የተካተቱ ምክረሃሣቦች ብዛት በቁጥር |
| 2.2.ማረሚያ ቤቶች፣ ፓሊስ ጣቢያዎችና ማቆያ ማዕከላት ላይ ክትትል ማድረግ | • ስልታዊና መደበኛ ክትትል ማከናወን<br>• በማረሚያ ቦታዎች በሂደት የሚታዩትን የሰብአዊ መብት አጠባበቅ መሻሻሎችን ወይም ማሽቆልቆሎችን መገምገም/መመዘን እና መሰነድ<br>• የክትትል ግኝቶችንና ምክረ ሃሳቦችን ይፋ ማድረግ<br>• ምክረሃሳቦች ተግባራዊ እንዲደረጉ ውትወታ/ግፊት ማድረግ | በእስር ላይ/በጥበቃ ስር ያሉ ሰዎች መብቶች ጥበቃ እና አያያዝ ተሻሽሏል፤ | • ግልጽ ምክረ ሃሳቦች ያካተቱ የክትትል ሪፖርቶች ብዛት በቁጥር<br>• በእስር ላይ/በጥበቃ ስር ያሉ ሰዎችን ጥበቃና እንክብካቤ ለማሻሻል በባለግዴታዎች የተወሰዱ እርምጃዎች ብዛት በቁጥር |
| 2.3.በግለሰቦች /በቡድኖች ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች በአግባቡ መቀበል፣ መመርመርና መፍትሄ መስጠት | • አቤቱታዎችን መሰረት በማድረግ አለያም በራስ ተነሳሽነት የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን መመርመር እና ምላሽ መስጠት<br>• ውጤታማ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት<br>• የምርመራ አፈጻጸም መመሪያዎችን መከለስና ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ<br>• ለአቤቱታዎች መፍትሄ ለመስጠት እና ውጤታማ የሪፈራል ሥርዓት ለመዘርጋት ከስትራቴጂያዊ አጋሮች ጋር መተባበር እና መደጋገፍ<br>• አግባብነት ያለው የግጭት አፈታት ስልት አጠቃቀምን ማራመድ<br>• የምርመራ ግኝቶችና ምክረ ሃሳቦች ተግባራዊነት መከታተል<br>• የአቤቱታ አቅራቢዎች እርካታን በየጊዜው መገምገም | በሰብአዊ መብት ጥሰቶች ዙሪያ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች ውጤታማ መፍትሄ ተሰጥቷል | • ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመፍቻ አማካይ ጊዜ በመቶኛ<br>• የተሰጡ ውጤታማ መፍትሄዎች ብዛት በቁጥር |
| 2.4.በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን መከታተልና መመርመር | • የኮሚሽኑን በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ምላሽ የመስጠት ብቃት ማጠናከር<br>• በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወቅት ስልታዊ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ማድረግ<br>• ሊከሰቱ ስለሚችሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ቅድመ | የአስቸኳይ ሁኔታዎች ምላሽ አሰጣጥ ሂደት ዉስጥ በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ማዕከላዊ ቦታ | ኮሚሽኑ በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ምላሽ እንዲሰጥ ለማስቻል የተዘረጋ ተዛማጅ፣ አግባብነት ያለው፣ ውጤታማና ዘላቂ የሆነ ሥርዓት ብዛት በቁጥር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ማስጠንቀቀያ / አስቀድሞ መከላከያ ሥርዓት ማዘጋጀትና መተግበር<br>• የምርመራ ግኝቶችንና ምክረ ሃሳቦችን ይፋ ማድረግ | እንዲይዝ ተደርጓል | |
| 2.5.የአመራርና ሠራተኛ አቅም ግንባታ | • የሥልጠና ፍላጎት ጥናት ማድረግ<br>• የአመራርና ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• ሜንተሪንግ ኮቺንግና የሥራ ላይ ሥልጠናን ጨምሮ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን | በሰብአዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ ረገድ ተፈላጊ ብቃት እና ክህሎት ያለው አመራርና ሠራተኛ መኖር | በየሥራ ክፍሉና በየጾታው የሰለጠነ አመራርና ሠራተኛ ብዛት በቁጥር |

## የፕሮግራም መስክ 3፡ የሴቶችና ሕጻናት መብቶች

**የስትራቴጂው ዓላማ፡-** የሴቶችና ሕጻናት መብቶች ተራምደዋል ተከብረዋል እንዲሁም ጥሰቶች ውጤታማ ምላሽ አግኝተዋል፤

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (Outcomes) | የአፈጻጸም አመልካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 3.1 በሴቶችና ሕጻናት መብት ሁኔታዎች እንዲሁም ተዛማጅ ዘላቂ የልማት ግቦች ላይ ጥናት/ምርመራ ማድረግና ሕዝባዊ መድረኮችን ማከናወን፣ ለጥሰቶችም ውጤታማ ምላሽ እንዲኖር መስራት | • የሴቶችና ሕጻናት መብቶች የሚመለከቱ የሕግ ማዕቀፎች እና በአተገባበር ረገድ ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት የሚያስችል ምርምር/ጥናት ማድረግ<br>• ሕዝባዊ መድረኮችን ማከናወን<br>• ስልታዊ የሆኑ የሴቶችና ሕጻናት መብት ጥሰቶች ላይ ምርመራ ማድረግ<br>• የአቋም መግለጫ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ<br>• የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ውትወታ/ግፊት ማድረግ እና ማራመድ<br>• የሕግ አውጪ አካላትን፣ መንግስትን እና ሌሎች ተቋማትን ማማከር | የሕግ ማዕቀፎች እና አተገባበራቸው ከሕገ መንግስታዊ፣ ከዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት መመዘኛዎች/ደረጃዎች ጋር እንዲጣጣሙ በኮሚሽኑ የተሰጡ ምክረ ሃሳቦች በአግባቡ ተካተዋል | • በጉዳዩ ላይ አግባብነት ያላቸው የተፈተሹ ምክረ ሃሳብ የቀረበባቸው ሕጎች ብዛት በቁጥር<br>• በሚመለከታቸው አካላት ተዛማጅ ሕጎችን ለማሻሻል የሚያሳዩት የጎለበተ ተነሳሽነት |
| 3.2 በመንግስትና በግል ተቋማት ዘንድ የሴቶችና ሕጻናት መብቶች መከበራቸውን መከታተል እና እንዲከበሩ ውትወታ/ግፊት ማድረግ | • የዖታ እኩልነት እንዲሁም የሴቶችና ሕጻናት መብቶች ዙሪያ ያለውን ሁኔታና አፈጻጸምን በሚመለከት ክትትል ማድረግ<br>• አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ የሰብአዊ መብት ሥርዓቶች ጋር በትብብር መስራት<br>• የዖታ እኩልነትንና የሴቶችና ሕጻናት መብቶች ያሉበትን ሁኔታ የሚገልፅ ሪፖርቶችን ማዘጋጀትና ይፋ ማድረግ<br>• ብሔራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ መመዘኛዎችን መሰረት ያደረጉ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የውትወታ ስራ መስራት<br>• ያልፀደቁ ስምምነቶች እንዲፀድቁ የውትወታ/ ግፊት ስራ መስራት | ባለግዴታዎች የዖታ እኩልነት እንዲሁም የሴቶችና ሕጻናት መብቶችን በማክበር እና በማስከበር ረገድ መሻሻል አሳይተዋል | • በኮሚሽኑ የተሰሩ የውትወታ/ግፊት ስራዎች ብዛት በቁጥር<br>• በሚገባ የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው የክትትል ሪፖርቶችና ምክረሃሳቦች ብዛት በቁጥር |
| 3.3 የሴቶችና ሕጻናት መብቶችን ማራመድ፣ ሕዝባዊ ንቅናቄ | • የባለመብቶችንና ባለግዴታዎችን ግንዛቤ ማሳደግ<br>• ማህበረሰቡን በሴቶችና ሕጻናት እና ሴቶች መብቶች ዙሪያ ማነቃነቅ | • ባለመብቶች መብታቸውን ለመጠየቅ የሚያስችላቸውን ብቃት አጎልብተዋል | • ሴቶች እና ሕፃናት መብቶቻቸውን እንዲጠይቁ ለማብቃት የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መፍጠር እና ማብቃት | • መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክ እና መደበኛ መገናኛ ብዙሃን ማሰራጨት<br>• ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተጋገዝ ኮንፈረንሶችን፣ ሴሚናሮችን፣ የፓኔል ውይይቶችን እና ሌሎች የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት | • ባለግዴታዎች የሴቶች እና ሕጻናት መብቶችን በማክበር እና ማስከበር ረገድ የጎለበተ ግንዘቤ እና ተሳትፎ አላቸው | ተነሳሽነቶች ብዛት በቁጥር<br>• በባለመብቶች የቀረቡ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሪፖርቶች በመቶኛ<br>• የባለግዴታዎችን አቅምና ተነሳሽነትን ለማሳደግ የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ ተነሳሽነቶች ብዛት በቁጥር |
| 3.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር/መተጋገዝና አጋርነት መፍጠር | • መድረኮች መፍጠር፣ ድጋፍ ማድረግ እና አብሮ መስራት<br>• የሴቶችና ሕጻናት መብቶችን በሚያራምዱ የጋራ መድረኮች መሳተፍ<br>• በዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ መድረኮች መሳተፍ | ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር መሥራትና ብሎም የጥረቶችን ህብር መጎልበት፤ | በአጋርነት ከኮሚሽኑ ጋር በሴቶችና ሕፃናት መብቶች ላይ የሚሰሩ የባለድርሻ አካላት ብዛት በቁጥር |
| 3.5 የአመራርና ሠራተኞች አቅም ግንባታ | • የሥልጠና ፍላጎት ጥናት ማድረግ<br>• የአመራርና ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• የሥራ ላይ ሥልጠናን ሜንተሪንግ ኮቺንግን ጨምሮ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን | በሴቶች እና ሕጻናት መብቶች ረገድ ተፈላጊ ብቃት እና ክህሎትና ያለው አመራርና ሠራተኛ መኖር፤ | ብቁ እና የሰለጠነ አመራርና ሰራተኛ በቁጥር |

## ፕሮግራም መስክ 4፡ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች

**የስትራቴጂው ዓላማ፡-** የአካል ጉዳተኞችና የአረጋውያን መብቶች ተራምደዋል፣ ተከብረዋል እና የመብቶች ጥሰት ውጤታማ በሆነ መልኩ ምላሽ አግኝቷል፡፡

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (Outcomes) | የአፈጻጸም አመላካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 4.1 በአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች ዙሪያ ጥናት/ምርመራ ማድረግ፤ የሕዝባዊ ውይይት መድረክ ማዘጋጀት እና ለጥሰቶች ውጤታማ ምላሽ እንዲኖር መስራት | • አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን በሚመለከቱ የሕግ ማዕቀፎች እና በአተገባበር ረገድ ያለውን ክፍተት ለማወቅ የሚያስችል ጥናት/ምርምር ማድረግ<br>• መዋቅራዊ/ስልታዊ የሆኑ የመብት ጥሰቶች ላይ ምርመራ ማድረግ<br>• የኮሚሽኑን አቋም ይፋ ማድረግ<br>• ለመብት ጥሰቶች ተገቢ ምላሽ/መፍትሔ እንዲኖር ውትወታ ማድረግ<br>• ሕግ አውጪውን፣ መንግስትን እና ሌሎች ተቋማትን ማማከር | የሕግ ማዕቀፎች እና አተገባበራቸው ከሕገ መንግስታዊ፤ ከዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ደረጃዎች /መመዘኛዎች ጋር እንዲጣጣሙ በኮሚሽኑ የተሰጡ ምክረ ሃሳቦች በአግባቡ ተካተዋል፤ | • ተቀባይነት ያገኙና በአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች ዙሪያ ለውጥ ያመጡ በኮሚሽኑ የተሰጡ ምክረሃሳቦች ብዛት በቁጥር<br>• የሚመለከታቸው አካላት ተዛማጅ ሕጎችን ለማሻሻል የሚያሳዩት የጎለበተ ተነሳሽነት |
| 4.2 በመንግስትና በግል ተቋማት ዘንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጡ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብት መመዘኛዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ክትትል | • የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን መብቶች አከባበር ደረጃን ለመመዘን የሚያስችል ክትትል ማድረግ<br>• በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስርዓቶች ጋር መስራት<br>• የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች አፈጻጸም ደረጃን የሚያሳይ ዘገባ ማዘጋጀትና ለሕዝብ ይፋ ማድረግ<br>• ከዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ግፊት/ ውትወታ ማድረግ | ባለግዴታዎች የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶችን በማክበር እና በማስከበር ረገድ መሻሻል አሳይተዋል | • በሚገባ የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው የክትትል ሪፖርቶችና ምክረሃሳቦች ብዛት በቁጥር<br>• በኮሚሽኑ የተሰሩ የውትወታ/ግፊት ስራዎች ብዛት በቁጥር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማድረግ እና እንዲከበሩ መወትወት/ግፊት ማድረግ | • ያልጸደቁ ስምምነቶች እንዲጸድቁ እና እንዲተገበሩ ውትወታ ማድረግ | | |
| 4.3 የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶችን ማራመድ/ማስፋፋት እንዲሁም መብቶችን በተመለከተ ሕዝባዊ ንቅናቄ እና ብቃትን መፍጠር | • የባለግዴታዎች እና የባለመብቶችን ግንዛቤ ማሳደግ<br>• ማህበረሰቡን ማነቃቃት<br>• በመብት ዙሪያ መረጃዎችን በኤሌክትሮኒክና መደበኛ ሚዲያዎች ማስራጨት<br>• ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ኮንፈረንሶችን፣ ሴሚናሮችን፣ የፓኔል ውይይቶችን እና ሌሎች የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት | ባለመብቶች መብታቸውን ለመጠየቅ የሚያስችላቸው ብቃት ጎልብቷል፤ ባለግዴታዎች የአካል ጉዳተኛና አረጋውያን መብቶችን በማክበር እና በማስከበር ረገድ የላቀ ግንዛቤ እና ተነሳሽነት መኖር | • ባለመብቶችን ለማብቃት የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ ተነሳሽነቶች ብዛት በቁጥር<br>• በባለመብቶች የቀረቡ የመብት ጥሰት አቤቱታ በመቶኛ<br>• የባለግዴታዎችን አቅምና ተሳትፎ ለማሳደግ የረዱ ውጤታማ ተነሳሽነቶች ብዛት በቁጥር<br>• በሚመለከታቸው ባለግዴታዎች የተወሰዱ እርምጃዎች ብዛት በቁጥር |
| 4.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር መተጋገዝ/ትብብር እና አጋርነት መፍጠር | • የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶችን የሚመለከቱ መድረኮች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ማነሳሳት፣ መደገፍ እና መካፈል<br>• የጋራ ተግባራት እና እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ<br>• በዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ መድረኮች መሳተፍ | ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር የላቀ ትብብር እና የጥረቶች ህብር መጎልበት | • ኮሚሽኑ የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ሰብአዊ መብቶች ላይ በአጋርነት አብሮ የሚሰራቸው የባለድርሻ አካላት ቁጥር |
| 4.5 የአመራርና ሠራተኞች አቅም ግንባታ | • በኮሚሽኑ ውስጥ አካል ጉዳተኝነትን የሚመለከት ኦዲት/ምርመራ ማከናወን<br>• የሥልጠና ፍላጎት ጥናት ማድረግ<br>• የአመራርና ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• ሜንተሪንግ ኮቺንግና የሥራ ላይ ሥልጠናን ጨምሮ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን፤ | በአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን መብቶች ረገድ ብቃት እና ክህሎት ያለው አመራርና ሠራተኛ መኖር | ብቁ እና የሰለጠነ አመራርና ሰራተኛ ብዛት በቁጥር |

## የፕሮግራም መስክ 5፡- የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞችና ፍልሰተኞች መብቶች

**የስትራቴጂው ዓላማ፡-** የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ስደተኞችና ፍልሰተኞች መብቶች ተራምደዋል፤ ተከብረዋልና የመብት ጥሰቶች ተገቢውን ምላሽ አግኝተዋል፤

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (Outcomes) | የአፈጻጸም አመላካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 5.1 የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ፍልሰተኖች እና ስደተኞች መብቶች ዙሪያ ጥናት/ምርመራ ማድረግ፤ የሕዝባዊ መድረኮች ማዘጋጀት እና ጥሰቶች ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ | • የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ፍልሰተኖች እና ስደተኞች መብቶች በተመለከተ ያለውን የሕግ ማዕቀፎችና አተገባበር ክፍተት የሚጠቁሙ ጥናቶች ማድረግ<br>• መዋቅራዊ/ስልታዊ ጥሰቶች ላይ ምርመራ ማድረግ<br>• የኮሚሽኑን የአቋም ይፋ ማድረግ<br>• ውጤታማ የሆነ የእርምት እርምጃ/ካሳ እንዲኖር ማራመድና መወትወት<br>• ትኩረት የሚሹ የመብቶች ጉዳዮችን በተመለከተ ምላሽ ለማስገኘት ሕግ አውጪውን፣ መንግስትን እና ማናቸውን ሌላ ተቋማትን ማማከር | የሕግ ማዕቀፎች እና አተገባበራቸው ከሕገ መንግስታዊ፣ አህጉራዊ እና ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች የጥራት ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ናቸው፤ | • በኮሚሽኑ ተፈትሸው ግልጽ ምክረ ሃሣብ የተሰጠባቸው ተዛማጅ ሕጎች ብዛት በቁጥር<br>• የሚመለከታቸው አካላት ተዛማጅ ሕጎችን ለማሻሻል የሚያሳዩት የጎለበተ ተነሳሽነት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5.2 በመንግስትና በግል ተቋማት የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ፍልሰተኖችና ስደተኞች መብቶች አከባበር ላይ ክትትል እና ውትወታ /ግፊት ማድረግ | • የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ፍልሰተኞችና ስደተኞች መብቶች አከባበርና አተገባበር ያለበትን ደረጃ ለመፈተሽ የሚያስችል ክትትል ማድረግ<br>• በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስርዓቶች ጋር መስራት<br>• ወቅታዊ ዘገባን ማዘጋጀትና ለሕዝብ ይፋ ማድረግ<br>• ሕገ መንግስታዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ደረጃዎች/መመዘኛዎች ጋር የተጣጣሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ውትወታ/ግፊት ማድረግ<br>• የሚመለከታቸው ስምምነቶችን ለማፅደቅና ነባሮቹን ለመተግበር የውትወታ ስራ መስራት | ባለግዴታዎች የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ፍልሰተኖች እና ስደተኞች መብቶችን በማክበር እና በማስከበር ረገድ መሻሻል አሳይተዋል | • በሚገባ የተተገበሩ የክትትል ሪፖርቶችና ምክረሃሳቦች ብዛት በቁጥር<br>• በኮሚሽኑ የተሰሩ የውትወታ/ግፊት ስራዎች ብዛት በቁጥር |
| 5.3 የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ፍልሰተኖች እና ስደተኞች መብቶችን ማራመድ፣ ሕዝባዊ ንቅናቄ መፍጠር እና ማብቃት | • የባለመብቶችንና ባለግዴታዎችን ግንዛቤ ማሳደግ<br>• ማህበረሰቡን ማነቃቃት<br>• የሰብአዊ መብቶች መረጃዎችን በማህበራዊ እና መደበኛ መገናኛ ብዙሃን ማሰራጨት<br>• ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ኮንፈረንሶች፣ ሴሚናሮች፣ የፓኔል ውይይቶች እና ሌሎች የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት | • ባለመብቶች መብታቸውን ለመጠየቅ የሚያስችላቸው ብቃት ጨምሯል<br>• የባለግዴታዎች ግንዛቤ እና መብቶቹን ለማክበር እና ለማስከበር ቁርጠኝነት አላቸው | • ባለመብቶችን ለማብቃት የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ ተነሳሽነቶች ብዛት በቁጥር<br>• በባለመብቶች ሪፖርት የተደረጉ የመብቶች ጥሰቶችን በመቶኛ<br>• ባለግዴታዎችን አቅምና ተነሳሽነት ለማሳደግ የተተገበሩ ውጤታማ ተነሳሽነቶች ብዛት በቁጥር<br>• በሚመለከታቸው ባለግዴታዎች የተወሰዱ እርምጃዎች ብዛት በቁጥር |
| 5.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር መተጋገዝ /ትብብር እና አጋርነት መፍጠር | • መድረኮች እንዲፈጠሩ ማድረግ፤ መደገፍ እና መካፈል<br>• መብቶችን በሚያራምዱና በሚጠብቁ የጋራ መድረኮች መሳተፍ<br>• በዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ መድረኮች መሳተፍ | ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር መሥራት ብሎም የጥረቶች ህብር ጎልብቷል፤ | ኮሚሽኑ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ፍልሰተኞችና ስደተኞች መብቶች ላይ በአጋርነት አብሮ የሚሰራቸው የባለድርሻ አካላት ብዛት በቁጥር |
| 5.5 የአመራርና ሠራተኞች አቅም ግንባታ | • የሥልጠና ፍላጎት ጥናት ማድረግ<br>• ለአመራርና ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• ሜንተሪንግ ኮቺንግና የሥራ ላይ ሥልጠናን ጨምሮ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን | ብቃት እና ክህሎት ያለው አመራርና ሠራተኛ መኖር | ብቁ እና የሰለጠነ አመራርና ሰራተኛ ብዛት በቁጥር |

## የፕሮግራም መስክ 6:- የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች

**የስትራቴጂው ዓላማ:-** የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ተራምደዋል፤ ተከብረዋል እና የመብት ጥሰቶች ተገቢውን ምላሽ አግኝተዋል፤

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (Outcomes) | የአፈጻጸም አመላካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 6.1 የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ዙሪያ ጥናት /ምርመራ ማድረግ፤ ሕዝባዊ መድረኮች ማዘጋጀት እና ለጥሰቶች ተገቢ ምላሽ እንዲሰጥ ውትወታ/ግፊት ማድረግ | • በሕግ ማዕቀፎችና አተገባበር ረገድ ያለውን ክፍተት ለመለየት የሚያስችል ጥናት/ምርምር ማድረግ<br>• መዋቅራዊ/ስልታዊ የሲቪልና ፖለቲካ መብት ጥሰቶች ላይ ምርመራ ማከናወን<br>• የኮሚሽኑን አቋም ይፋ ማድረግ<br>• ለመብት ጥሰቶች ተገቢ ምላሽ አንዲሰጥ ውትወታ/ግፊት ማድረግ<br>• የሕግ አውጭውን፣ መንግስትን እና ሌሎች ተቋማትን ማማከር | የሕግ ማዕቀፎች እና አተገባበራቸው ከሕገ መንግስቱ፣ አህጉራዊና ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች ጋር የተጣጣሙ ናቸው፤ | • በኮሚሽኑ ተፈትሸው ግልጽ ምክረ ሃሣብ የተሰጠባቸው ተዛማጅ ሕጎች ብዛት በቁጥር<br>• የሚመለከታቸው አካላት ተዛማጅ ሕጎችን ለማሻሻል የሚያሳዩት የጎለበተ ተነሳሽነት |
| 6.2 የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች መመዘኛዎች በመንግስትና በግል በተቋማት ስለመከበሩ ክትትል ማድረግ እና እንዲከበሩ ግፊት/ ውትወታ ማከናወን | • የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች አከባበር እና አተገባበር ያለበትን ደረጃን ለመመዘን የሚያስችል ክትትል ማከናወን<br>• በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አሠራር መሳተፍ<br>• የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ ዘገባ ማዘጋጀትና ለሕዝብ ይፋ ማድረግ<br>• ከሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች ጋር የተጣጣሙ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ግፊት/ውትወታ ማከናወን<br>• ያልጸደቁ ስምምነቶች እንዲጸድቁ እና እንዲተገበሩ ግፊት/ውትወታ ማከናወን | ባለግዴታዎች የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶችን በማክበርና በማስከበር ረገድ መሻሻል አሳይተዋል | • በሚገባ የተተገበሩ የክትትል ሪፖርቶችና ምክረሃሳቦች ብዛት በቁጥር<br>• በኮሚሽኑ የተሰሩ የውትወታ/ግፊት ስራዎች ብዛት በቁጥር |
| 6.3 የሲቪልና ፖለቲካ መብቶችን ማስፋፋት፣ ሕዝባዊ ንቅናቄ መፍጠር እና ማብቃት | • የባለመብቶችንና ባለግዴታዎችን ግንዛቤ ማሳደግ<br>• ማህበረሰቡን ማነቃቃት<br>• የሰብአዊ መብቶች መረጃን በኤሌትሮኒክስና በመደበኛ መገናኛ ብዙሃን ማሰራጨት<br>• ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተጋገዝ/በመተባበር ኮንፈረንሶች፣ ሴሚናሮች፣ የፓኔል ውይይቶች እና ሌሎች የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት | ባለመብቶች መብታቸውን ለመጠየቅ የሚያስችላቸው ብቃት ጨምሯል የባለግዴታዎች ግንዘቤ ጎልብቷል፣ መብቶቹን በማክበር እና በማስከበር ረገድ ተነሳሽነታቸው ጨምሯል | • ባለመብቶች ለማብቃት የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ ስራዎች ብዛት በቁጥር<br>• በባለመብቶች ሪፖርት የተደረጉ የመብት ጥሰቶች በመቶኛ<br>• የባለግዴታዎችን አቅምና ተሳትፎ ለማሳደግ የተሰሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ ስራዎች ብዛት በቁጥር<br>• በሚመለከታቸው ባለግዴታዎች የተወሰዱ እርምጃዎች ብዛት በቁጥር |
| 6.4 ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር መተጋገዝ፣ አጋርነት መፍጠር | • መድረኮች እንዲፈጠሩ ማድረግ፤ መደገፍ እና መካፈል<br>• መብቶችን በሚያራምዱና በሚጠብቁ የጋራ መድረኮች መሳተፍ<br>• በዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ መድረኮች መሳተፍ | ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር መሥራትና የጥረቶች ህብርም ጎልብቷል | ኮሚሽኑ በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ዙሪያ በአጋርነት አብሮ የሚሰራቸው የባለድርሻ አካላት ብዛት በቁጥር |
| 6.5 የአመራርና ሰራተኞች አቅም ግንባታ | • የሥልጠና ፍላጎት ጥናት ማድረግ<br>• የአመራርና ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• ሜንተሪንግ ኮኦቺንግና የሥራ ላይ ሥልጠናን ጨምሮ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን | ተፈላጊው ብቃት እና ክህሎት ያለው አመራርና ሰራተኛ መኖር | ብቁ እና የሰለጠነ አመራርና ሰራተኛ ብዛት በቁጥር |

## የፕሮግራም መስክ 7:- የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ መብቶች

**የስትራቴጂው አላማ:** :የኢኮኖሚ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች (ኢሶባ) ተራምደዋል፣ተከብረዋል እና የመብት ጥሰቶች ተገቢውን ምላሽ አግኝተዋል፣

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (Outcomes) | የአፈጻጸም አመላካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 7.1.የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶች ዙሪያ ጥናት/ምርመራ ማድረግ፣ ሕዝብዊ መድረኮችን ማዘጋጀት እና ለመብት ጥሰቶች ተገቢ ምላሽ/የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ግፊት /ውትወታ ማድረግ | • የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊና መብቶችን በሚመለከቱ የሕግ ማዕቀፎች እና አተገባበር ረገድ ያለውን ክፍተት ለመፈተሽ የሚያስችል ጥናት/ምርምር ማድረግ<br>• ስልታዊ/መዋቅራዊ በሆኑ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብት ጥሰቶች ላይ ምርመራ ማድረግ<br>• የኮሚሽኑን የአቅዋም ለሕዝብ ይፋ ማድረግ<br>• ለመብት ጥሰቶች ተገቢ ምላሽ እንዲሰጥ ግፊት/ውትወታ ማድረግ<br>• ሕግ አውጭውን፣ መንግስትን እና ሌሎች ተቋማትን ማማከር | የሕግ ማዕቀፎችና አተገባበራቸው ከሕገ መንግስቱ፣ ከአህጉራዊ እና ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች/ ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ናቸው | • በኮሚሽኑ ተፈትሸው ግልጽ ምክረ ሃሣብ የተሰጠባቸው ተዛማጅ ሕጎች ብዛት በቁጥር<br>• የሚመለከታቸው አካላት ተዛማጅ ሕጎችን ለማሻሻል የሚያሳዩት የጎለበተ ተነሳሽነት |
| 7.2.የመንግስትና የግል ተቋማት አሰራር ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶች መመዘኛዎች /ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ስለመሆናቸው ክትትል ማድረግ እና እንዲከበሩ ውትወታ/ግፊት ማከናወን | • የኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶች ያሉበትን እና የአተገባበራቸውን ደረጃን ለመፈተሽ የሚያስችል ክትትል ማድረግ<br>• በአህጉራዊና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አሠራር መሳተፍ<br>• መብቶች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ ዘገባ ማዘጋጀትና ለሕዝብ ይፋ ማድረግ<br>• ከሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች እና ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ግፊት ማድረግ<br>• ያልጸደቁ ስምምነቶች እንዲጸድቁ እና እንዲተገበሩ ውትወታ ማድረግ | ባለግዴታዎች ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶችን በማክበር እና ማስከበር ረገድ መሻሻል አሳይቷል | • በሚገባ የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው የክትትል ሪፖርቶችና ምክረሃሳቦች ብዛት በቁጥር<br>• በኮሚሽኑ የተተገበሩ የግፊት ስራዎች ብዛት በቁጥር |
| 7.3.የኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶችን ማስፋፋት /ማራመድ፣ ሕዝባዊ ንቅናቄ መፍጠር እና ማብቃት | • የባለመብቶችንና የባለግዴታዎችን ግንዘቤ ማሳደግ<br>• ማህበረሰቡን ማነቃቃት<br>• ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ መብቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች በኤሌክትሮኒክስና መደበኛ መገናኛ ብዙሃን ማሰራጨት<br>• ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተጋገዝ/በመተባበር ኮንፈረንሶች፣ ሴሚናሮች፣ የፓኔል ውይይቶች እና ሌሎች የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀ | • ባለመብቶች መብታቸውን ለመጠየቅ የሚያስችላቸው ብቃት ጨምሯል<br>• የባለግዴታዎች ግንዘቤ ጎልብቷል፣ መብቶቹን በማክበር እና በማስከበር ረገድ ተነሳሽነታቸው ጨምሯል | • ባለመብቶች ለማብቃት የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ ስራዎች ብዛት በቁጥር<br>• በባለመብቶች ሪፖርት የተደረጉ የመብት ጥሰቶች በመቶኛ<br>• የባለግዴታዎችን አቅምና ተሳትፎ ለማሳደግ የተሰሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ ስራዎች ብዛት በቁጥር<br>• በሚመለከታቸው ባለግዴታዎች የተወሰዱ እርምጃዎች ብዛት በቁጥር |
| 7.4.ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር | • የትብብር መድረኮች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ማነሳሳት፣ | ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት | ኮሚሽኑ በኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶች ላይ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መተጋገዝና አጋርነት መፍጠር | መደገፍ እና አብሮ መስራት<br>• መብቶችን በሚያራምዱና በሚጠብቁ የጋራ መድረኮች መሳተፍ<br>• በዓለም አቀፍና አህጉራዊ መድረኮች ላይ መሳተፍ | ጋር የመሥራት እና የጥረቶች ህብር ጎልብቷል፤ | በአጋርነት አብሮ የሚሰራቸው የባለድርሻ አካላት ብዛት በቁጥር |
| 7.5.የአመራርና ሰራተኞች አቅም ግንባታ | • የሥልጠና ፍላጎት ጥናት ማድረግ<br>• የአመራርና ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• ሜንተሪንግ ኮኦቺንግና፣ የሥራ ላይ ሥልጠናን ጨምሮ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናወን | ብቃትና ክህሎት ያላቸው አመራርና ሰራተኛ መኖር | ብቁ እና የሰለጠነ አመራርና ሰራተኖች ብዛት በቁጥር |

## የፕሮግራም መስክ 8፡- ውጤታማ ኮሙኒኬሽን እና አጋርነት

**የስትራቴጂው ዓላማ፡-** ዕውቅናን እንዲሁም ከሕብረተሰቡ እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ትብብርን በማሳደግ ከፍ ያለ ውጤት የሚያመጣ የሰብአዊ መብቶች ተግባራትን ማከናወን

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (Outcomes) | የአፈጻጸም አመላካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 8.1. የተቋማዊ እውቅናን በማጎልበት ሰብአዊ መብቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች፣ ሰነዶች እና አገልግሎቶች ተደራሽነት ማሳደግ | • የተሟላ የኮሚኒኬሽንና ብራንዲንግ ስትራቴጂ ማዘጋጀት<br>• የአጋርነት ስትራቴጂ ማዘጋጀት እና መተግበር<br>• የመረጃ፣ ኮሚኒኬሽን እና ቴክኖሎጂን (ኢኮቴ) እንዲሁም ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም የአገልግሎት ተደራሽነትን፤ አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ፤ ማሳደግ<br>• የሚዲያ ክትትል ማድረግ<br>• ዘገባዎችን እና ሌሎች ሰነዶችን በተለያዩ ቋንቋዎች እና ማየት ለተሳናቸው እንዲመቹ አድርጎ ማዘጋጀት | ኢሰመኮ ሰብአዊ መብቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን እንዲሁም አገልግሎቶችን ተደራሽነትን አሻሽሏል፤ | • የተዘጋጁና የተተገበሩ አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ የሆኑ አዲስ ሥርዓቶች ብዛት በቁጥር<br>• በተሻሻለው ስርዓት በኩል የተሻለ አገልግሎት እና መረጃ ያገኙ ሰዎች/ተቋማት ብዛት በቁጥር |
| 8.2.የዕውቀት አያያዝና አስተዳደር | • የዕውቀት አያያዝና አስተዳደርን ተቋማዊ ማድረግ<br>• ሁሉን አቀፍ እና ተአማኒ የሆነ የዕውቀት ማሸጋገሪያ ማቴሪያሎች ማዘጋጀት፣ ማጋራት፣ ጥቅም ላይ ማዋል<br>• ቴክኖሎጂን በመጠቀም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ፍሰትና ደህንነት ማረጋገጥ፤ | ኢሰመኮ መረጃን እና አዝማሚያዎችን በመጠቀም ለአስተዳደር የሚጠቅም መረጃን የሚያመነጭ የመረጃ ስርዓት አለው፤ | አግባብነት ያላቸው እና ውጤታማ የሆኑ አዲስ ስርዓቶች፣ መሣሪያዎች እና ተግባራዊ የተደረጉ መረጃን የሚያስተዳድሩና የሚያመነጩ የቴክኖሎጂ መፍትሄዎች ብዛት በቁጥር |
| 8.3.በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለመሥራት የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶችንና ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎችን ማዘጋጀት/ማዳበር | • የአገልግሎት አሰጣጥን ለማጎልበት እና የጥራት ሥራ አመራር ሥርዓትን ተቋማዊ ለማድረግ ኢኮቴን መጠቀም<br>• የሰራተኛን የዲጂታል ክህሎት ማሳደግ<br>• የኤሌትሮኒክስ መድረኮችንና መሳሪያዎችን ለኢ-ትምህርት ጥቅም ላይ ማዋል<br>• ሚስጥራዊነት ያላቸው መረጃዎችን ፍሰትና ደህንነት የሚያስጠብቅ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ማቅረብ<br>• ውጤታማነትና ቅልጥፍናን ለማሳደግ የሚያስችሉ | ኢሰመኮ በኢኮቴ የተደገፉ ሥርዓቶችን፣ መሳሪያዎችን እና መፍትሔዎችን በመጠቀም ፕሮግራሞቹንና አገልግሎቶቹን አሻሽሏል | • ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችን ለማሻሻል የተጠቀምንባቸው የሥርዓቶች፣ መሳሪያዎች እና መፍትሔዎች ብዛት በቁጥር<br>• የኮሚሽኑ ባለጉዳዮች ጥቅም ላይ በዋሉት ሥርዓቶች፣ መሳሪያዎች እና መፍትሔዎች ያላቸው የእርካታ ደረጃ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ቴክኖሎጂዎችንና የአሠራር ሥርዓቶችን መጠቀም<br>• የኮሚሽኑን ስራ ቀጣይነት የሚያረጋግጡ ዕቅዶችን ማውጣትና መተግበር | | |
| 8.4 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት | • ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ የቅርብ ግንኙነትን መዘርጋት እና ማጠናከር<br>• ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት እንዲሁም ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማትን ጨምሮ መተባበርና መደጋገፍ<br>• በብሔራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች፣ ትስስሮች፣ የጋራ ስራወች እንደአስፈላጊነቱ መሳተፍ<br>• ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስርዓቶች ጋር መስራት | ኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶች ስራን ከብሔራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ጋር አቀናጅቶ ይሰራል፤ | • የአጋሮች ብዛት በቁጥር<br>• የውጤታማ አጋርነት እና ትብብር ብዛት በቁጥር<br>• የተደራጁ የጋራ መድረኮች ብዛት በቁጥር<br>• በባለድርሻ አካላትና በባለመብቶች ለኮሚሽኑ የሚሰጡ ዕውቅናዎች መጨመር<br>• የጋር ስራዎች ብዛት በቁጥር |

## የፕሮግራም መስክ 9:- የተቋማዊ ሪፎርም፣ አቅም ግንባታና ዘላቂነት/ቀጣይነት

**የስትራቴጂው ዓላማ፡** ኮሚሽኑ የተቋቋመለትን ዓላማ እና ተልዕኮ ለማሳካት የሚመጥን ነፃነት፣ ውጤታማነት፣ ብቃትና ዘላቂነት ያለው ብቃት አዳብሯል፤

| ስትራቴጂዎች | ዋና ተግባራት | የግብ ስኬቶች (Outcomes) | የአፈጻጸም አመላካቾች (Indicators) |
|---|---|---|---|
| 9.1. ለለውጥ አመራር እና ለውጤታማ የውሳኔ አሰጣጥ የሚጠቅሙ ስርዓቶችን ማጠናከር | • ግልጽ የሆነ የአመራር እና የውሳኔ ሰጪ ስርዓቶችን ማዘጋጀት<br>• በለውጥ አመራር ላይ ለአስተዳደር ሰራተኞች የስልጠና እና የልምድ ልውውጥ ማዘጋጀት | የተጠናከረ የአመራር እና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቶች እና ስልቶች ተፈጥሯል | በአዲስ መልክ የተዘጋጁ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ስርዓቶች ብዛት በቁጥር |
| 9.2. ኢሰመኮ ብቃት ያለው እና የተለያዩ ሰራተኞችን የመሳብ፣ የማዳበር እና የማቆየት አቅም እንዲኖረው አጠቃላይ የሰው ሃብት አስተዳደር ሥርዓቱን ማሻሻል | • አዲሱን ተቋማዊ መዋቅር ተግባራዊ ማድረግ<br>• ገበያውንና የተቋሙን አቅም ያገናዘበ በብቃት እና በአፈጻጸም ላይ የተመሠረተ የክፍያና ማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፤<br>• የጾታ እኩልነትና የአካል ጉዳተኞች ማካተትን ጨምሮ የተሻሻለ የሰው ሃብት አስተዳደር ፖሊሲ እና ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፤<br>• ለአዳዲስ ሰራተኞች የመግቢያ ሥልጠና መስጠት<br>• የአቅም ግንባታ ፍላጎቶችን ግምገማ ማካሄድ እና የአመራርና ሰራተኞች አቅም ግንባታ እቅዶች መተግበር፤ | ኮሚሽኑ ተነሳሽነት ያላቸው የተለያዩ ሰራተኞችን መሳብ እና ማቆየት የሚችል ግልጽ፣ ፍትሃዊ እና ቀልጣፋ የሰው ሃብት አስተዳደር ስርዓት ያለው የበቃ ተቋም ሆኗል፤ | • በኮሚሽኑ ሪፎርም የተሳቡና ለአንድ ዓመት የቆዩ ብቃት ያላቸው ሰራተኞች ብዛት በቁጥር<br>• በዋና የስራ ተግባራትና በባለሙያነት የተቀጠሩ ሴት ሰራተኞች በመቶኛ<br>• የተቀጠሩ አካል ጉዳተኛ ሰራተኞች በመቶኛ |
| 9.3. የፋይናንስና አስተዳደር ሥርዓቱን በማሻሻልና ግልጽና ዘመናዊ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ቅልጥፍናን ማሳደግ | • የፋይናንስ ፖሊሲዎችን እና የአፈጻጸም መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ማስተዋወቅ እና መተግበር<br>• በአዲስ መልኩ የፀደቀው የፋይናንስ ፖሊሲዎችና የአፈጻጸም መመሪያዎች ላይ ሰራተኞችን ማሰልጠን | • አዳዲስ የአሠራር ሥርዓቶች፣ የፖሊሲ መተግበሪያ መሳሪያዎች እና ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች መተግበር ጀምረዋል፤<br>• የትግበራ ልህቀት | • የተዘጋጁ እና የተተገበሩ አዳዲስ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የአሰራር ስርዓቶች እና ስልቶች ብዛት በቁጥር<br>• የሰራተኞች እርካታ ደረጃ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | አድጓል፤ | |
| 9.4. **ሰራተኞችን የሚያሳትፍ እና አፈጻጸማቸውን የሚያሳድግና በኮሚሽኑ እሴቶች ላይ የተመሰረተ ተቋማዊ ባሕል መዘርጋት** | • የብቃት ማዕቀፍ ማዘጋጀት እና መተግበር<br>• የኮሚሽኑን እሴቶችና የስራ ባሕል ለማሳደግ የሚያስችል ግንዛቤ እና ቁረጠኝነት ማሳደግ<br>• የስራ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት መተግበር<br>• በአፈጻጸም ምዘናውን ብቃትን መሰረት ካደረገ የማበረታቻ ሥርዓት ጋር ማስተሳሰር | የጋራ እሴቶች እና የተቋማዊ ባህል ያላቸው ከፍተኛ አፈፃፀም፣ ተነሳሽነት እና ንቁ ተሳትፎ ያላቸው  ሠራተኞች አሉ፤ | • የሚፈለገውን የአደረጃጀት ባህል ለማሳደግ በአዲስ መልኩ የተገነቡ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ስርዓቶች እና ስልቶች ብዛት በቁጥር<br>• የአፈጻጸም ደረጃዎችን የሚያሟሉ ሰራተኞች በመቶኛ |
| 9.5. **ተደራሽ እና ምቹ የቢሮ አካባቢ መፍጠር** | • የኮሚሽኑ ቢሮዎች ለሕዝብ እና ለአካል ጉዳተኞች ያላቸውን የተደራሽነት ደረጃ መገምገም<br>• የኮሚሽኑ የሥራ ቦታዎች በቀላሉ ተደራሽ እና ለትራንስፖርትም አመች መሆናቸውን ማረጋገጥ<br>• ምቹ የሥራ ሁኔታዎችን መፍጠር | ተደራሽና ምቹ የሆነ የሥራ ቦታ ተፈጥሯል | • ተደራሽ እና ምቹ የሆኑ የኢሰመኮ ጽ/ቤቶች ብዛት በቁጥር |
| 9.6. **ሃብት ማሰባሰብን ማጎልበት** | • የሃብት ማሰባሰቢያ ስትራቴጂ ማዘጋጀትና መተግበር<br>• ከልማት አጋሮች ጋር ስትራቴጂያዊ አጋርነት መፍጠርና ማጠናከር<br>• የበጀት መጠን እንዲጨምርና በወቅቱም እንዲለቀቅ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ የፋይናንስ ምንጮችን ጋር በቅርበት መስራት | ፋይናንስን የመቆጣጠርና ሃብትን የማሰባሰብ  አቅም ተገንብቷል፤ | • በአዲስ መልኩ ተዘርግተው ተግባራዊ የሆኑ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የፋይናንስ ቁጥጥር እና የሃብት ማሰባሰብ ስርዓቶች ብዛት በቁጥር<br>• የጎለበተ የሃብት መጠን |